Education for Justice
A project of the Minnesota Legal Services Coalition

Fact Sheet
Amharic

# ለጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ እንዴት ማመልከት እንደሚቻል

(How to Apply for Temporary Protected Status)




ይህ የእውነታ ወረቀት ጊዜያዊ የከለላ ሁኔታ ስለተባለ የአጭር ጊዜ የስደተኝነት ሁኔታ ይናገራል። አንዳንድ ጊዜ TPS ይባላል። ይህ የእውነታ ወረቀት የሚነግርዎት፡-

- ለጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ማን ማመልከት እንደሚችል።
- የጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ካገኙ ምን ማድረግ እንደሚችሉ።
- የጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ማመልከቻ ደረጃዎች።

To read this fact sheet in other languages, go to: lawhelpmn.org

Mid-Minnesota Legal Aid, Southern Minnesota Regional Legal Services, The Advocates for Human Rights, and the Volunteer Lawyers Network. It was supported by funding from the State of Minnesota Department of Human Services.

# ጊዜያዊ ከለላ ሁኔታን ማን ሊያገኝ ይችላል።

## ጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ምንድን ነው?

**የአጭር ጊዜ የስደተኝነት ሁኔታ ነው።** የዩኤስ መንግስት ከአገርዎ የመጡ ሰዎች ወደ ቤት መመለሳቸው አደገኛ ነው ብሎ ካሰበ ለእሱ ማመልከት ይችላሉ። አደገኝነቱ በተፈጥሮ አደጋ፣ ጦርነት ወይም የእርስ በርስ ግጭት ሊሆን ይችላል። የዩኤስ መንግስት ሰዎች ለጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ብቁ የሆኑባቸውን ሁሉንም አገሮች ዝርዝር ይይዛል። ዝርዝሩ በUSCIS ድህረ ገጽ ላይ ይገኛል: uscis.gov/humanitarian/temporary-protected-status በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉት አገሮች ይለወጣሉ።

**ጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ከፈለጉ ለእሱ ማመልከት አለብዎት።** የትውልድ አገርዎ በዝርዝሩ ውስጥ ስላለ ብቻ ወድያዉ አያገኙም። የዩኤስ መንግስት ወደ ሀገር ቤት መሄዱ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው ብሎ እስኪያስብ ድረስ ጊዜያዊ ከለላ ያላቸው ሰዎች በአሜሪካ ውስጥ ሊኖሩ እንድሁም በህጋዊ መንገድ ሊሰሩ ይችላሉ።

**ጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ለአንድ ሰው ቋሚ የኢሚግሬሽን ደረጃ አይሰጥም።** ነገር ግን የትውልድ አገርዎ በዝርዝሩ ላይ ከቀጠለ ጊዜያዊ ከለላ ሁኔታዎን ማደስ ይችሉ ይሆናል። በዩናይትድ ስቴትስ ረዘም ላለ ጊዜ ለመቆየት ከፈለጉ የኢሚግሬሽን ጠበቃን ያነጋግሩ።

## ለጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ብቁ ነኝ?

ለጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ለማመልከት የሚያስፈልጉዎት 4 ነገሮች አሉ። እነዝህን መሟላት ያስፈልጋል፦

1. **ዩኤስ ለጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ በዝርዝሩ ላይ ካስቀመጠው ሀገር መሆን።** ያ ማለት የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት ሰዎች ወደዚያች ሀገር መመለሳቸው ደህንነታቸዉ የተጠበቀ እንዳልሆነ ወስኗል። ማመልከቻ በሚያስገቡበት ጊዜ ዜግነትዎን የሚያረጋግጡ ሰነዶች ያስፈልጉዎታል። ጥምር ዜግነት ካሎት፣ ለጊዜያዊ ጥበቃ ሁኔታ ከማመልከትዎ በፊት የኢሚግሬሽን ጠበቃን ያነጋግሩ።

2. **2. የትውልድ አገርዎ በዝርዝሩ ውስጥ ሲገባ በአካል በዩናይትድ ስቴትስ መኖር አለበት።** ይህ “አካላዊ መገኘት” ይባላል። እንዲሁም ለተዘረዘረው ጊዜ በዩኤስ ውስጥ የመኖሪያ ቦታ መያዝ አለቦት። ይህ “በቀጣይነት መኖር” ይባላል። በብቁነት ቀናት አከባብ ወይም በብቁነት ቀናት ውስጥ ከዩኤስ ውጭ ከተጓዙ ለጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ከማመልከትዎ በፊት ከኢሚግሬሽን ጠበቃ ጋር ይነጋገሩ።

3. **በማመልከቻው ከመጨረሻ ቀን በፍት ያመልክቱ።** የዩኤስ መንግስት ለጊዜያዊ ጥበቃ ሁኔታ ማመልከቻዎችን የሚቀበልበት አጭር ጊዜ ነዉ። የማመልከቻውን የመጨረሻ ቀን በUSCIS ድህረ ገጽ በ: uscis.gov/humanitarian/temporary-protected-status ያስታውቃሉ። ከማለቂያው ቀን በፊት ማመልከት አለቦት። ቀነ-ገደቡ ካመለጠዎት የኢሚግሬሽን ጠበቃን ያነጋግሩ።

4. **ያለቀ የወንጀል ሪከርድ ይኑርዎት።** ከሁለት በላይ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ሊኖሩዎት አይችሉም። አነስተኛ ስርቆት ወይም ያለመኪና ኢንሹራንስ ማሽከርከር በደል ናቸው። ወንጀል ከመፈጸምዎ በፊት፣ ከፖሊስ ወይም ከጠበቃ ጋር ለመስማማት ከመስማማትዎ ወይም ዋቢ ከመክፈልዎ በፊት የኢሚግሬሽን ጠበቃን ያነጋግሩ። በማንኛውም ወንጀል ከተከሰሱ፣ ለጊዜያዊ ከለለ ሁኔታ ከማመልከትዎ በፊት ከኢሚግሬሽን ጠበቃ ጋር ይነጋገሩ።

## ጊዜያዊ ከለላ ካገኘሁ ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል?

**እንደሁኔታዉ።** የትውልድ አገርዎ በዝርዝሩ ውስጥ እስከአለ ብቻ ጊዜያዊ ከለላ ለማግኘት ብቁ ነዎት። አንድ አገር ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ በዝርዝሩ ውስጥ ሊቆይ ይችላል። በእዚያ ሀገር ውስጥ የተፈጥሮ አደጋ ከተፈጠረ ለ3 ወራት ያህል በዝርዝሩ ውስጥ ሊኖር ይችላል። በእዚያ ሀገር ውስጥ ረዥም ጦርነት ካለ ለዓመታት በዝርዝሩ ውስጥ ሊኖር ይችላል። የትውልድ ሀገርዎ እንደገና ወደ ዝርዝሩ በተጨመረ ቁጥር ሁኔታዎን ማደስ አለቦት።



**ለምሳሌ፤ ሶፊያ በጦርነት ምክንያት ዩክሬንን ለቅቃለች።.**

በጦርነት ምክንያት የዩክሬን ሀገር ከሚያዝያ 2022 እስከ ጥቅምት 2023 ድረስ በጊዜያዊ ከለላ(TPS) ዝርዝር ውስጥ ገብታለች። ሶፊያ በዩክሬን ተወለደች። በጥር 2023 ትታ ወደ ሚኒሶታ መጣች። ሶፊያ ለ TPS አመልክታለች። እስከ ጥቅምት 2023 ድረስ TPS ተሰጥቷታል። በጥቅምት 2023፣ የዩኤስ መንግስት የዩክሬንን ቦታ እስከ ሚያዝያ 2025 ድረስ አራዘመ። ሶፊያ ሁኔታዋን ለመጠበቅ ለ TPS እና የስራ ፍቃድ እንደገና ማመልከት አለባት።

## በጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ዝርዝር ውስጥ የትኞቹ አገሮች ናቸው ያሉት?

ዝርዝሩ ይቀየራል። የትውልድ አገርዎ በዝርዝሩ ውስጥ እንዳለ ለማወቅ፡-

1. ወደ USCIS ድህረ ገጽ ይሂዱ፡ uscis.gov/humanitarian/temporary-protected-status
2. ዝርዝሩን ለማየት "በአሁኑ ጊዜ ለ TPS የተመደቡ አገሮች" ላይ ጠቅ ያድርጉ።

ጊዜያዊ ጥበቃ የሚደረግለት ሁኔታ ካለህ፣ የዩኤስ መንግስት የትውልድ ሀገርህን ጊዜ በዝርዝሩ ላይ እያራዘመ መሆኑን ለማየት ድህረ ገጹን በየቀኑ ይመልከቱ። ጊዜያዊ ከለላሁኔታዎ ከማለፉ 3 ወራት በፊት ማረጋገጥ ይጀምሩ።

## ለጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ለማመልከት ቀነ-ገደቡ መቼ ነው?

ይህ የማመልከቻ ቀነ-ገደብ ለእያንዳንዱ ሀገር የተለያየ ነው። **ቀነ-ገደቡ ካመለጠዎት የኢሚግሬሽን ጠበቃን ያነጋግሩ።** የማመልከቻውን የመጨረሻ ቀን ለማግኘት፡-

1. ወደ USCIS ድህረ ገጽ ይሂዱ: uscis.gov/humanitarian/temporary-protected-status
2. ዝርዝሩን ለማየት "በአሁኑ ጊዜ ለ TPS የተመደቡ አገሮች" ላይ ጠቅ ያድርጉ።
3. አገርዎን ይምረጡ። ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያመለክቱ ከሆነ "የምዝገባ ጊዜ" የመጨረሻው ቀን ነው። የእርስዎን TPS እያደሱ ከሆነ "የዳግም ምዝገባ ጊዜ" የመጨረሻው ቀን ነው።

ይህ ሰንጠረዥ ለጊዜያዊ ጥበቃ ሁኔታ የተለያዩ ቀኖችን እና ቀነ-ገደቦችን ይገልጻል። እያንዳንዱ ምን ማለት እንደሆነ ያብራራል።

| ምድብ | ምን ማለት ነው |
|---|---|
| **TPS Designated Through:**<br>TPS የተመደበው በ፡ | TPS እዚህ ሀገር ላሉ ሰዎች የሚያበቃበት ቀን። **ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚያመለክቱ ሰዎች <u>እና</u> TPS የሚያድሱ ሰዎችን ይመለከታል።** |
| **Re-Registration Period:**<br>ዳግም ምዝገባ ጊዜ፡- | የእርስዎን TPS ለማደስ ማመልከት ያለብዎት ቀን። ሁሉም ሀገር ይህ ቀን አይኖረውም።. **ይህ አስቀድሞ TPS ላላቸው ሰዎች ነው።** |
| **Registration Period:**<br>የምዝገባ ጊዜ፡- | **ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያመለክቱ ከሆነ** ለ TPS ማመልከት ያለብዎት ቀን። |
| **Employment Authorization Document (EAD) Auto-Extended Through:**<br>የቅጥር ፍቃድ ሰነድ (EAD) በራስ-የተራዘመ በ፡ | በአሁኑ ጊዜ የስራ ፍቃድ ካለዎት፣ TPS ን በሚያድሱበት ጊዜ የስራ ፍቃድዎ እስከታድስ ድረስ የሚሰራበት ቀን ነው።. ነገር ግን ማመልከቻዎ በመጠባበቅ ላይ እያለ መስራትዎን መቀጠል ይችላሉ። **ይህ አስቀድሞ TPS ላላቸው ሰዎች ነው።** |
| **Continuous Residence in United States Since:**<br>በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያለማቋረጥ መኖር ከ፡- | ለማመልከት ከዚህ ቀን ጀምሮ በዩናይትድ ስቴትስ እየኖሩ መሆን አለበት። ወደ ሌላ ሀገር ሄደዉ መመለስ አይችሉም። **ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚያመለክቱ ሰዎች <u>እና</u> TPS የሚያድሱ ሰዎችን ይመለከታል።** |
| **Continuous Physical Presence in United States Since:**<br>በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ቀጣይነት ያለው አካላዊ መገኘት ከ፡- | ከዚህ ቀን ጀምሮ ለ"አጭር፣ ላልተወሰነ እና ንፁህ" ጉዞዎች ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭ ብቻ ነው መጓዝ የሚችሉት። **ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚያመለክቱ ሰዎች <u>እና</u> TPS የሚያድሱ ሰዎችን ይመለከታል።** ከዚህ ቀን ጀምሮ ከዩኤስ ውጭ የተጓዙ ከሆነ፣ ለጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ከማመልከትዎ በፊት ከኢሚግሬሽን ጠበቃ ጋር ይነጋገሩ። |
| **TPS Designation Date:**<br>TPS የተመደበበት ቀን፡- | የዩኤስ መንግስት ይህንን አገር ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ TPS ዝርዝር ያከለበት ቀን። **ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚያመለክቱ ሰዎች <u>እና</u> TPS የሚያድሱ ሰዎችን ይመለከታል።** |
| **Current TPS Designation Date:**<br>የአሁኑ የTPS ስያሜ ቀን፡- | የዩኤስ መንግስት ለዚች ሀገር በ TPS ዝርዝር ውስጥ በድጋሚ የተረጋገጠበት ቀን።. ሁሉም ሀገር ይህ ቀን አይኖረውም። **ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚያመለክቱ ሰዎች <u>እና</u> TPS የሚያድሱ ሰዎችን ይመለከታል።** |

## ጊዜያዊ ከለላ ካገኘሁ መሥራት እችላለሁ?

**አዎ፣ <u>ለስራ</u> ፈቃድ ካመለከቱ።** ጊዜያዊ ከለላ ያለው ሁኔታ ካሎት ወዲያውኑ ለመስራት ፈቃድ አያገኙም። ለጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ሲያመለክቱ በተመሳሳይ ጊዜ ለሥራ ፈቃድ ማመልከት አለብዎት። በዚህ የእውነታ ወረቀት ክፍል "ለማመልከት ደረጃዎች" ውስጥ ለሥራ ፈቃድ ለማመልከት መመሪያዎች አሉ። ጊዜያዊ ከለላ ሁኔታዎን ማደስ ከፈለጉ በተመሳሳይ ጊዜ የስራ ፈቃድዎን ማደስ አለብዎት። ማመልከቻዎ በሚገመገምበት ጊዜ መስራቱን መቀጠል ይችላሉ።

## ከኢሚግሬሽን ጠበቃ ጋር መነጋገር አለብኝ?

ከጠበቃ ጋር ሳይነጋገሩ ጊዜያዊ ጥበቃ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ። እነዝህ ካሉ ከማመልከትዎ በፊት ጠበቃን ማነጋገር ጥሩ ነው፡-:

- ጥምር ዜግነት ከአለዎት። ምሳሌ፡- ሶማሌ ሆነዉ የተወለዱት ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ከሆነ።
- የማመልከቻው ቀነ-ገደብ ከአመለጠት።
- በማንኛውም ወንጀል ተፈርዶቦት ከሆነ።
- ወንጀል መፈፀሙዎን እንድናዘዙ ወይስ ላጠፉት ጥፋት በገንዘብ እንድቀጡ ተጠይቀዉ ከሆነ።

- በብቃት ቀናት አከባብ ወይም  በብቃት ቀናት ውስጥ ከዩኤስ ውጭ ከተጓዙ።
- በዩናይትድ ስቴትስ በቋሚነት መኖር እና መሥራት የሚፈልጉ ከሆነ።
- ለጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ብቁ መሆንዎን በተመለከተ ጥያቄዎች ከአሉዎት።

## የትውልድ አገሬን ከ TPS ዝርዝር ውስጥ ቢያወጡት ምን ይከሰታል?

የትውልድ አገርዎን TPS ካላቸው አገሮች ዝርዝር ውስጥ ካወጡት ወዲያውኑ ጠበቃን ያነጋግሩ! ለሌሎች የእምግሬሽን እፎይታ ዓይነቶች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ጠበቃ ስላለዎት አማራጮችዎ ሊያነጋግርዎት ይችላል። ለሀገርዎ TPSን የሚያዘገይ ወይም የሚያቆም ማንኛውም ሙግት ካለ ጠበቃዎ ሊነግሮት ይችላል።

## የሚረዳኝ ጠበቃ የት ማግኘት እችላለሁ?

በLawHelpMN.org ላይ ነፃ ጠበቆችን እና የህግ ክሊኒኮችን ይፈልጉ። ነፃ ጠበቆች በጣም ተፈላጊ ናቸው። ስለጠየቁ ብቻ የነጻ ጠበቃ ዋስትና አይሰጥዎትም። ለመገናኘት ወደ 200 ዶላር መክፈል የሚችሉ ከሆነ ከግል ጠበቃ ጋርም መነጋገር ይችላሉ።

# የማመልከት ደረጃዎች

## ለጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

ለሥራ ፈቃድ ለማመልከት 4 ደረጃዎች አሉ።

### ደረጃ 1. ቅጽ I-821 ይሙሉ።

ቅጹን ለማግኘት ወደ uscis.gov/i-821 ይሂዱ ወይም የQR ኮድን ይቃኙ። መልሶችዎን ይተይቡ ወይም በጥቁር ቀለም ይፃፉ። መልሶትን በእንግሊዝኛ ይጻፉ።

### ደረጃ 2. ከማመልከቻዎ ጋር ለመላክ ሰነዶችን ይሰብስቡ።

ለጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ብቁ መሆንዎን የሚያረጋግጡ ሰነዶችን መላክ አለቦት። **ማመልከቻ ውድቅ የሚደረገበት በጣም የተለመደው  ምክንያት ሰዎች ማረጋገጫን ስለማይልኩ ነው።** ከጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ማመልከቻዎት ጋር 7 ነገሮችን ይላኩ፡-

- ☐ **የተጠናቀቀ ቅጽ I-821**

- ☐ **ማንነትዋን የሚያረጋግጥ 1 ሰነድ ቅጂ።** ሰነዱ በዩናይትድ ስቴትስ ወይም በሌላ ሀገር መንግስት የተሰጠ መሆን አለበት። ሰነዱ በእንግሊዝኛ ካልሆነ፣ መተርጎም አለብዎት። ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-
    - የእርስዎን ምስል፣ ስም እና የልደት ቀን የሚያሳይ ፓስፖርት
    - የልደት የምስክር ወረቀት ከፎቶ መታወቂያ ጋር
    - ቪዛ በውጭ ቆንስላ የተሰጠ
    - መልከቻዎን እያደሱ ከሆነ የቀደሞ የስራ ፍቃድ ሰነድ  ***ወይም***
    - የብሄራዊ መታወቂያ ሰነድ ከፎቶዎ ጋር

☐ **አገርዎ በጊዜያዊ ከለላ ሁኔታ ዝርዝር ውስጥ መካተቱን የሚያረጋግጥ የ1 ሰነድ ቅጂ።** ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- የእርስዎን ምስል፣ ስም እና የልደት ቀን የሚያሳይ ፓስፖርት **ወይም**
- የልደት የምስክር ወረቀት ከፎቶ መታወቂያ ጋር

☐ **በዩናይትድ ስቴትስ መኖሩዎን የሚያሳዩ ከ1 እስከ 3 ሰነዶች ቅጂዎች።** ያለዋት ሰነድ 1 ብቻ ከሆነ እርሱኑ መላክ ይችላሉ። 3 መላክ የተሻለ ነዉ። ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-

- የኪራይ ስምምነት
- የቤት ማስያዣ ሰነዶች
- የሕክምና መዝገቦች
- ለእርስዎ ወይም ለልጆችዎ የትምህርት ቤት መዛግብት (ስምዎ በመዝገቦች ላይ መኖር አለበት)
- የቅጥር መዝገቦች
- ከጎረቤቶች፣ ከሀይማኖት ማህበረሰብ፣ የበጎ ፈቃደኝነት ስራዎች ደብዳቤዎች
- በዩ ኤስ ውስጥ ካደረጓቸው ግዢዎች የተገኙ ደረሰኞች።
- የገንዘብ ዝውውሮች መዝገቦች
- የስልክ መዝገቦች
- በዩኤስ አድራሻ የተቀበሉት ደብዳቤ **ወይም**
- ፎቶዎች፣ ቀን የታተመበት ከሆነ እንድሁም በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥየተነሱ ከሆነ

☐ **የተሞላ ቅጽ I-765 (ለሥራ ፈቃድ ማመልከት ከፈለጉ ብቻ)** ጊዜያዊ ከለላ ያላቸው ሰዎች እንዲሠሩ ይፈቀድላቸዋል፣ ነገር ግን ለሥራ ፈቃድ ማመልከት አለባቸው። ቅጽ I-765 ይሙሉ። በ uscis.gov/i-765 ላይ ይገኛል። ቅጽ I-765 ከጊዜያዊ ከላለ ማመልከቻ ጋር መላክ አለቦት። **ለየብቻ አትላኩት።** LawHelpMN ለሥራ ፈቃድ እንዴት ማመልከት እንደሚቻል የሚናገር የእውነታ ወረቀት አለው። ወደ lawhelpmn.org/self-help-library/fact-sheet/how-get-permission-work-minnesota ይሂዱ።

☐ **ሁለት ተመሳሳይ 2 ኢንች x 2" የፓስፖርት ፎቶግራፎች (ለሥራ ፈቃድ የሚያመለክቱ ከሆነ ብቻ)።** እንደ CVS፣ Wal-Mart ወይም Target ባሉ መደብሮች የፓስፖርት ፎቶዎችን ማንሳት ይችላሉ።

☐ **ክፍያ ወይም ክፍያ የመሰረዝ ማመልከቻ።** የገንዘብ ማዘዣ ይላኩ ወይም ያረጋግጡ። የገንዘብ ማዘዣ ለመክፈል ተመራጭ መንገድ ነው። ከጥር 2025 ጀምሮ ያሉት ክፍያዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። ክፍያዎች ሊለወጡ ይችላሉ። ማመልከቻዎን በፖስታ ከመላክዎ በፊት ትክክለኛውን ክፍያ መላክዎን ለማረጋገጥ የUSCIS website ይመልከቱ።

- **ለጊዜያዊ ጥበቃ ሁኔታ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያመለክቱ ከሆነ:** ለማመልከት 50 ዶላር ክፍያ እና 30 ዶላር የባዮሜትሪክ ክፍያ አለ። ለስራ ፍቃድ የሚያመለክቱ ከሆነ ተጨማሪ የ520 ዶላር ክፍያ አለ።

- **ለጊዜያዊ ከላለ ሁኔታ ለማደስ የሚያመለክቱ ከሆነ:** የ30 ዶላር የባዮሜትሪክስ ክፍያ አለ። ለስራ ፍቃድ የሚያመለክቱ ከሆነ ተጨማሪ የ$520 ክፍያ አለ።

- **ክፍያውን መክፈል ካልቻሉ ለክፍያ መቋረጥ ያመልክቱ።** ሁለቱም ጊዜያዊ ጥበቃ ሁኔታ እና ለሥራ ፈቃድ ክፍያ ክፍያዎች ለማመልከት ተመሳሳይ I-912 form ቅጽ ይጠቀሙ። LawHelpMN’s ድህረ ገጽ ለክፍያ ማቋረጥ እንዴት ማመልከት እንደሚቻል የእውነታ ወረቀት አለው። ወደ: lawhelpmn.org/self-help-library/fact-sheet/immigration-fee-waivers-0

## ደረጃ 3. የማመልከቻዎን ቅጂ ያዘጋጁ።

የእርስዎን ቅጽ I-821 እና የማመልከቻ ሰነዶችን ቅጂ ያድርጉ። ቅጂውን ለመዛግብትያስቀምጡ።

## ደረጃ 4 ማመልከቻዎን ወደ ዩኤስ ዜግነት እና ኢሚግሬሽን አገልግሎት (USCIS) ይላኩ።

- ማመልከቻውን ከአገርዎ ጋር በሚዛመደው አድራሻ ይላኩ። ወደ: uscis.gov/humanitarian/temporary-protected-status ይሁዱ። “በአሁኑ ጊዜ ለ TPS የተመደቡ አገሮች” ላይ ጠቅ ያድርጉ። የፖስታ አድራሻውን ለማግኘት አገርዎን ይምረጡ።
- ማመልከቻዎን በፖስታ ሲልኩ መከታተያ ይግዙ። ሲደርስ ማስረጃ ወይም ደረሰኝ ማግኘትዎን ያረጋግጡ።

***Fact Sheets are legal information NOT legal advice. See a lawyer for advice.***
*Don’t use this fact sheet if it is more than 1 year old. Ask us for updates, a fact sheet list, or alternate formats.*

**© 2025 Minnesota Legal Services Coalition.** This document may be reproduced and used for non-commercial personal and educational purposes only. All other rights reserved. This notice must remain on all copies. Reproduction, distribution, and use for commercial purposes are strictly prohibited.